# ወይ ፍንክች !

ጠኋት በልጅነት ፣ ቃል የገባሁለት
ኢትዮጵያዊነቱን ፣ የመሰከርኩለት
ከማንም ከምንም ፣ በልጦ የሚከበር
የእምነት ፣ እዳ አለብኝ ፣ አብሮኝ የሚቀበር ።

የጓዶች አደራ ፣ ከመቃብር ሆኖ
ይጮሃል ፣ ይጣራል ፣ ከምን ጊዜም ፣ ገንኖ
ዛሬም ፣ ታገል ይላል ፣ ጫካ ፣ ግባ ፋኖ
ሞተን ሳናልቅማ ፣ አይቀር ተወጥኖ
ጩኸት ቢበረክት ፣ አይቀርም ታፍኖ ።

አብረውኝ ተጉዘው ፣ መንገድ የወደቁ
በግፍ በጭካኔ ፣ በፋሽስት ያለቁ
ዛሬም አልደረቀ ፣ ትኩስ ነው ፣ ደማቸው
መቼ ተረሱና ፣ አፈር ቢጫናቸው
አሰሱም ፣ ገሰሱም ፣ ይዛበትባቸው ።

ከሰማይ ከምድር ፣ የከበደ አደራ
ተሸክሞ ያለ ፣ ቋሚ ባለተራ
በደሙ የከፈለ ፣ ተነስ ሲል ፣ ሲጣራ
አርማውን አንስቶ ፣ ችቦውን ያበራ
ዛሬም ፣ ኢሕአፓ አለ ፣ ጽናቱ የሚያኮራ ።

የእምነት እዳ ፣ አለብን ፣ በአላማ ልንጸና
ሞቶ ፣ ላኖረን ጓድ ፣ ለዚያ ፣ ቆራጥ ጀግና
እውን ፣ ሆኖ ህልሙ ፣ የተዋደቀለት
ከግብ ልናደርሰው ፣ ቃል የገባንለት
አለብን አደራ ፣ ጠኋት የተዘራ
አጭደን ፣ አልወቃነው ፣ መች ገባ ፣ ጎተራ ።

በታጋይ ደም ፣ ታጥቦ ፣ የጠራ ፣ የነጣ
ተስፋ የማይቆርጠው ፣ ባባጣ ጎርባጣ
እምነቱን ፣ ማተቡን ፣ ጸንቶ የዘለቀ
የኢሕአፓ ፣ ልጅ ነው ፣ ጥንትም የታወቀ።

ታግሎ መጣልና ፣ ታግሎ ፣ መውድውቁንም
የኢሕአፓ ጀግና ፣ ያውቅቀዋል ፣ ጥንቱንም
መታገል የሚሻ ፣ ታግሎ ፣ ያስመሰክራል
መቼ ፣ በአየር ሞገድ ፣ በጽሁፍ ያቅራራል
የወረቀት ነብር ፣ ያየር ሞገድ ፣ ታጋይ
ምርኮኛም ፣ ቁስለኛም ፣ አላሰየም ግዳይ ።

ፋሽስቱ ተነስቶ ፣ ዛሬ ቢንጠራራ
ተኩላ ግብራበሩን ፣ ሊያደራጅ ቢጠራ
ጩኸት ቢበረክት ፣ እሪታው ቢደራ
እነ አባ ፣ ኮስትሬ ፣ አለን ለምንጠራ
ወይ ፍንክች ፣ ወይ ንቅንቅ ፣ ትግላችን ሳይጠራ ።

ታዛቢው … February 10, 2012